# በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢ.ሕጤ.ኢ.

ታህሳስ 2014 ቅጽ 5 ቁጥር 9

በኢ.ሕጤ.ኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## ኢንስቲትዩቱ ከቤንሽ.ኤ.ኢ. አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በመጠቀም የሕብረተሰብ ጤና ምርምርን ለማሻሻል የሚያስችል የ3 አመት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።



ኢትዮጵያ/ ስፔን የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት (ኢ.ሕ.ጤ.ኢ) እና መሰረቱን ስፔን ያደረገው ቤንሺ.ኤ.ኣይ መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም አርቲፊሻል ኢንተለጀንስንና ማሽን ለርኒንግ በመጠቀም የህብረተሰብ ጤና ምርምሮችን ለማገዝ የሚያስችል ስምምነት ተፈራርመዋል።የመግባቢያ ሰነዱ ዓላማ በኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ምርምር ስራና ውጤቶችን በዘመናዊ እውቀቶች ለማገዝ ያለመ ሲሆን ለ3 ዓመት የሚቆይ ነው።

ዘመናዊ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ በሀገር አቀፍ ደረጃ በምግብ እና ስነ ምግብ ምርምሮች ላይ ለመተግበር ዝግጅት ሲደረግ የመጀመሪያ ጊዜ ነው። የኢ.ሕ.ጤ.ኢ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና አሰራሮችን በመጠቀም መረጃን መሰረት ያደረገ ምርምር፡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን እንዲሁም ስትራቴጂዎችን በማጎልበት የሕብረተሰብ ጤናን ለማሻሻል የሚያስችለው ስምምነት ሲሆን በቢል እና ሚሊንዳ ጌትስ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ለትርፍ ያልተቋቋመው ቤንሺ.ኤ.ኣይ ከተሰኘ ተቋም ጋር በጋራ የሚሰራ ነው።

መግባቢያ ሰነዱ የሚከተሉትን ሠፊ የትብብር ስራዎች ያጠቃልላል።

## ግለለሰሰብን መሰረት ያደረገ የኤች አይቪ ቅኝት አመታዊ የግምገማ መድረክ ተጠናቀቀ



ግለሰሰብን መሰረት ያደረገ የኤች አይቪ ቅኝት አመታዊ የግምገማ መድረክ ከ አዲስ አበባ፣ ከአፋር፣ ከአማራ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ከድሬዳዋ፣ ከሀረሬ፣ ከሶማሌ፣ ከጋምቤላ፣ ከኦሮሚያ፣ ከሲዳማ እንዲሁም የተለያዩ አጋር ድርጅቶች በተገኙበት በድሬዳዋ ከተማ ተካሄደ። በመድረኩም ከሁሉም ክልሎች የመጡ አካላት ግለሰብን መሰረት ያደረገ የኤች አይቪ ቅኝት አስመልክቶ የተሰሩ ስራዎች ሪፖርት አቅርበዉ ሰፋ ያለ ዉይይት ተካሂዶባቸዋል።

የጤና ሚኒስቴር አገልግሎትና ፕሮግራም ዘርፍ ድኤታ የሆኑት ዶ/ር ደረጀ ድጉማ በመድረኩ ተገኝተዉ እንደተናገሩት በኤች አይቪ ቅኝት ከጀመሩ ሀገራት ኢትዮጲያ ቀዳሚ ሀገር መሆኗን ጠቅሰዉ ስርጭቱ በተወሰኑ ከተሞች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ አሳሳቢ በመሆኑ ያለዉን ክፍተት ማጥበብ እና የመረጃ ጥራት አያያዝ ስራ

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# ጸረ-ሙስና እና የስራ ህገ-ደንብ ላይ ስልጠና ተሰጠ



የኢትዮጲያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የስነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና ዳይሬክቶሬት የስነ-ምግባር ምንነት፣ በሙስናና ብልሹ አሰራር፣ በመልካም አስተዳደር፣ ሙስና ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶች፣ የስራ ስነ-ምግባር እንዲሁም በመንግስት የስራ መመሪያ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በሱሉልታ ሃይሌ ሪዞርት ለኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች በቡድን በመከፋፈል ስልጠና ሰጠ።

በመድረኩም የሙስና አስከፊነትና ስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዙሪያ፣ በአገልግሎት ማሻሻያ ጥምረት አስተገባበር እንዲሁም በስራ ህገ-ደንብና አስፈላጊነት በሚሉ ርዕሶች ዙሪያ የሚመከለታቸው አካላት ሰፋ ያለ ስልጠና ሰጥተዋል። በቀረቡ ርዕሶች ዙሪያም በርካታ ሃሳብ አስተያየቶች ከተሳታፊዎች ተነስተው የሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ተሰጥቶ በቀጣይም ለሚቀሩ ኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ስልጠናው እንደሚሰጥ ከመድረክ ተገልጾ ስልጠናው ተጠናቋል።

# ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ጤና ባለሙያዎች የአሰልጠኞች





የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የህብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል / EOC/ ለጤና አደጋ ስጋት ተግባቦት እና ለማህበረሰብ ተሣትፎ ለፌዴራል ፖሊስ ጤና ባለሙያዎች በሁለት ዙር ከታህሳስ 11 እስከ 22 /2014 ዓ.ም በድሬዳዋ እና በጅማ ከተማ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰጠ ።

የስልጠናው ዋና አላማ በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መዋቅር ስር የሚገኙ የፖሊስ ማሰልጠኛ ተቋማት እና የስምሪት ካምፖች የተሰማሩ የፖሊስ አባላት ከስራቸው አንፃር በኮቪድ - 19 እና በሌሎችም የጤና አደጋ ወረርሽኞች ካላቸው ተጋላጭነት የተነሣ የመከላከል ስራዎችን ለማጠናከር የጤና ባለሙያዎችን የአሳልጠኞች ስልጠና በመስጠት በየተቋማቱ ለሚሰሩ የተለያዩ ሰራተኞች የተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጀ ነው።

ከሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የተወጣጡ በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ስር የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች በስልጠናው የተሳተፉ ሲሆን የጤና አደጋ ስጋት ተግባቦት ፣ የማህበረሰብ ተሣትፎ ፣ የመንግስት ተቋማት እና የሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የጤና አደጋ የሆኑትን ወረርሽኞችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል የተሻለ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ስልጠና መሆኑን ስልጠናውን ሲሰጡ ከነበሩ ባለሙያዎች መረዳት ተችሏል ።

## . . .ግለሰብን መሰረት ያደረገ

. . .ከገጽ 1 የዞረ

መጨመሩን ገልጸዋል::
በኢትዮጲያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኤች አይ ቪ ኤድስ እና ቲቢ በሽታ ምርምር ዳሬክቶሬት ዳሬክተር ወ/ሮ ሳሮ አብደላ በተደረገው ጥናት የተገኘውን ዉጤት ያቀረቡ ሲሆን በጾታ በመለየት 62% ከፍተኛ ድርሻ የሚይዙት ሴቶች መሆናቸዉን፣ የቀን ሰራተኞች 38.8% መሆናቸዉን፣ ከ15-19 የእድሜ ክልል ዉስጥ ያሉ ወጣቶች በቫይረሱ መያዛቸዉን ጥናቱ እንደሚያሳይ ገልፀዋል::
በጤና ሚኒስቴር የአገልግሎትና ፕሮግራም ዘርፍ ሚኒስቴር ድኤታ ጽ/ቤት ሀላፊ እና አማካሪ የሆኑት አቶ ፍቃዱ ያደታ በማጠቃለያዉ ተገኝተዉ እንደተናገሩት የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር ዋና ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቅሰዋል:: አክለዉም በሁሉም አካላት ሴቶችና ወጣቶችን መሰረት በማድረግ የሚሰሩ ዘርፈ ብዙ



ምላሽ ሰጪ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተጠናክረዉ መሰራት እንዳለባቸዉ ገልፀዋል::

በፕሮግራሙም በስተመጨረሻ በድሬዳዋ ከተማ የሚገኙት የመንግስት ሆስፒታሎች ተጎብኝተዋል::

## . . .ቤኒሺ.ኤ.አይ ጋራ ለመስራት

. . .ከገጽ 1 የዞረ

- ለኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ተመራማሪዎች በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት፡ በመጀመሪያ ምዕራፍ ለአንድ ሳምንት የሚቆይ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስና ማሽን ለርኒንግ ላይ ያተኮረ ስልጠና ለኢ.ሕ.ጤ.ኢ. አስተዳደር፣ ከ50 በላይ ለሚሆኑ ተመራማሪዎችና የጤና ባለሙያዎች በቤንሺ.ኤ.አይ አማካኝነት ይሰጣል::
- በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ መሳሪያዎች የታገዘ ምርምር መስራትና መረጃን የማጠናከር ስራ በተመረጡ የማሕበረሰብ የአመጋገብ ስርዓቶች ላይ ይከናወናል::
- በኢትዮጵያ ጥራታቸውን የጠበቁ የስነ-ምግብ ምርምሮችን ለመስራት በትብብሩ ወቅት የተሰሩ ውጤቶችን ይፋ ማድረግና አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን እንዲጠቀሙ ማበረታታትን ያጠቃልላል::

የኢ.ሕ.ጤ.ኢ የምግብ ሳይንስና እና የስነ ምግብ ምርምር ዳይሬክቶሬት ከቤንሺ.ኤ.ኣይ ጋር አብሮ በመሆን ይህን ስራ ይመራል:: በዋናነትም በአመጋገብ ችግሮችና የምግብ እጥረትን መሰረት ያደረጉ የምርምር ስራዎች ይሰራሉ:: መግባቢያ ሰነዱ በተፈረመበት ወቅት የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ዶ/ር ማስረሻ ተሰማ እንደተናገሩት “የኢ.ሕ.ጤ.ኢ ከቤንሺ.ኤ.ኣይ ጋር አብሮ መስራቱ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እና ማሽን ለርኒንግን በመጠቀም የስነ ምግብ የምርምር ስራዎችን ለማሳደግ ትልቅ ሚና አለው:: በተጨማሪም የስነ-ምግብ ምርምር ተመራማሪዎች የማሽን ለርኒንግ እና አርቴፍሽያል ኢንተለጀንስን በመጠቀም ጥራቱን የጠበቀ የምርምር ውጤቶችን እንዲያዘጋጁ ያግዛቸዋል::”

የቤንሺ.ኤ.ኣይ. መስራች እና ዋና ዳሬክተር የሆኑት ዶ/ር አፍሪካ ፔሬንዝ በበኩላቸው “ከኢ.ሕ.ጤ.ኢ ጋር አብረን የመስራት ትልቅ እድል በማግኘታችን እጅግ ደስተኞች ነን:: ከመንግስት ተቋሞች ጋር አብረን መስራታችን ዓለምአቀፍ የጤና ግቦችን በማሻሻል ረገድ ቁልፍ ሚና አለው:: የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ባለሞያዎቻችን ከኢ.ሕ.ጤ.ኢ ተመራማሪዎች የሚያገኙትን ተጨባጭ እውቀት ከዘመናዊው እውቀት ጋር በማቀናጀት ለዜጎች ለማህበረሰቡ እንዲሁም በሕብረተሰብ ጤና ዙሪያ ላይ መረጃን መሰረት ያደረጉ አዳዲስ መረጃዎችን ወደፊት ለማምጣት በጋራ እንሰራለን::”

በኢ.ሕ.ጤ.ኢ እና ቤንሺ.ኤ.ኣይ. የተደረገው ስምምነት ከ2022 እስከ 2024 የሚዘልቅ ይሆናል::